# አውደ ኢትዮጵያ

የካቲት15 2009 የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! እትም 23

## ለወቅታዊ ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ

### አቶ አክሎግ ልመንህ፤ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበራት ሊቀመንበር፤ በዋሽንግተን ዲሲ፤ ለህዝብ ካቀረቡት ንግግር የተቀነጨበ

የተከበራችሁ ተጋባዥ እንግዶች

የተከበራቹህ የዚህ ውይይት መድረክ አዘጋጆች በሙሉ

የተከበራችሁ በዚህ አዳራሽ የተገኛቹህ የዲሲ እና አከባቢው ነዋሪ ኢትዮጵያውያን በቅድሚያ፤ የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር አባላትን ወክዬ፤ በዚህ መድረክ ላይ ንግግር እንዳደርግና፤ ሀሳቤን ለእናንተ ለማካፈል፤ ከእናንተም ሀሳብን ለመካፈል፤ ስለተጋበዝኩኝ፤ ጋባዥዎቼን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።



ከእናንተ መሀል ተገኝቼ፤ በዛሬው ዕለት ለውይይት ማቅረብ የምፈልገው ሀሳብ፤ *ለወቅታዊ ጥያቄ፡ ተግባራዊ ምላሽ* የሚል ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለነፃነቱ፤ ለመብቱ፤ ለክብሩ፤ለሰላምና ብልፅግና፤ ከውጭ ወራሪ ሃይሎችም ይሁን ከአብራኩ ከበቀሉ አምባገነን ወገኖች ጋር ለዘመናት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሲታገልና ሲዋደቅ ቆይቷል፡፡ በዚህም ተጋድሎው፤ መስዋዕትነቱ ምንም ያህል የከፋ ቢሆንም፤ ጊዜው ያጥር ወይም ይረዝም እንደሆነ እንጂ፤ ሁልግዜም በአሸናፊነት ተወጥቶታል። በየወቅቱ የነበሩት ትግሎች ይዘታቸው የተለያየ ነበር፤ በመሆኑም የጠየቁት ህዝባዊ ምላሽም የተለየ ነበር።

የውጭ ጠላት ከሩቅም ይሁን ከቅርብ፤ ድንበር ተሻግሮ፤ ሀገር ወሮ፤ ህዝብ ለማስገበርና ለመግዛት፤ በሞከረበት አጋጣሚ ሁሉ፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን፤ ‹‹ጥራኝ ጫካው ጥራኝ ዱሩ›› ተባብለው፤ በአከባቢ የጎበዝ አለቃ በመደራጀት፤ ወራሪዎችን፤ በመግጠም ድል አድርገው፤ አንገት አስደፍተው አሳፍረው መልሰውታል። የውጭ ወራሪ በመጣ በማንኛውም ጊዜ፤ የዚህ ወይም የዛ ጎሳ፤ የዚህ ወይም የዛ ሃይማኖት ሳይባባል፤ ወንድ ሴቱ፤ ወጣት ሽማግሌው፤ በአንድነት ወደ ጦር ግንባር ይተማል። በውስጥ ጉዳይ ያልተግባቡ ቢኖሩ፤ በስልጣን ሽኩቻ፤ አንዱ ንጉስ ከሌላው ንጉስ፤ ለሞት የሚፈላለጉ ቢሆን እንኳን፤ በሽማግሌ እርቅ ይሆንና፤ በመተባበር በአንድነት ወራሪውን ይመክታሉ። በዚህም ምክንያት፤ አባቶቻችን ወቅቱ ለጠየቀው ጥያቄ፤ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት በመቻላቸው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ በቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ የጥቁር ሀገር እንድትሆን አስችለዋታል። ከዚያም ባሻገር፤ ለአፍሪቃ፤ ለጥቁር ህዝብ ዘርና ለነፃነት ታጋዮች በአጠቃላይ፤ እንደ እሩቅ ኮከብ የምታበራ የነፃነት ተምሳሌት፤ የተስፋ ብርሃን ሆናላቸዋለች። ቀጣዩ ትውልድም፤ የታፈረችና የተከበረች ሀገር ተረካቢ በመሆኑ፤ አንገቱን ቀና አድርጎ የሚኖር ሆኗል።

በቅርብ ጊዜ ታሪካችን ደግሞ፤ ከቀዳማዊ ሃይለሥላሴ አገዛዝ፤ እስከ ደርግ አስተዳደርና፤ አሁን ደግሞ፤ የወያኔ ጎሳዊ የሆነ ከፋፋይ ገዢ ድረስ፤ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለአንድነቱ፤ ለነፃነቱ፤ ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲያዊ አሰተዳደር፤ ለሰላምና ብልግና፤ ያላሰለሰ እልህ አስጨራሽ ህዝባዊ ትግል አድርጓል፤ በማድረግም ላይ ነው። በነዚህ ጊዜያትም፤ በቃኝ ደከመኝ፤ ሰለቸን፤ አይቻልም በሚሉ ጨለምተኛ መንፈሶች፤ ትግሉን አቁሞ፤ በፈቃዱ ተገዢ የሆነበት ጊዜ የለም፤ ወደፊትም አይኖርም።

> “በዚህ ወቅት ግለሰቦችም ይሁኑ ድርጅቶች የሚያደርጉት የታሪክ ሽሚያ የለም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፤ አነሰም በዛም ለትግሉ፡ የሚያደርገው አስተዋፅኦ የታሪክ ባለቤት ያደርገዋል። በጋራ ብርቱካንን ነፃ እናውጣ፤ በጋራ የህሊና እስረኞችን በአጣቃላይ ነፃ እናውጣ፤ በጋራ ትግላችን ሀገራችንን ነፃ እናውጣ። ኑ ተነሱ፤ እንነሳ፤ በጋራ ትግላችን ታሪክ እንስራ።”

ያለመታደል ሆኖ፤ በተለያዩ ምክንያቶች፤ አንድ አምባገነን ሲገረሰስ በምትኩ ሌላ አምባገነን ይተካል። አሁን ያለንበት ሁኔታ ይሄ ነው።

ወያኔ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ እንደተቆጣጠረ፤ የመጀመርያ ተግባሩ፤ ክህደት ነበር። ኤርትራን ከእናት ሀገሯ ኢትዮጵያ፤ ያለ ህዝብ ፍላጎት፤ በመለስና-ኢሳይስ መሃከል በተደረገ የጫካ ውል አማካኝነት፤ እንድትገነጠል ሆነች። በሂደቱም፤ ህዝብ ለህዝብ፤ ዘመድ ከዘመድ እንዲለያይ፤ ቤተሰብም እንዲበተን ሆኗል። ከዚያም ባሻገር፤ ኢትዮጵያችን ወደብ አልባ አገር እንድትሆን ተደረገ።

ወያኔ ኢትዮጵያ ላይ የሰራው፤ ሌላው ታሪክ ይቅር የማይለው የክህደት ወንጀል ደግሞ፤ ህዝብን በዘር፤ በጎሳና በቋንቋ በመለያየት፤ ሀገር ለመበትን በመቀመር፤ “…እስከ መገንጠል…” የሚል መርዘኛ አንቀፅ በህገ-መንግስቱ አስገባ፤ ፌደሬሽኑም፤ በዘር ላይ የተመሰረተ ሆነ። ህዝቡ ግን፤ ከመንግስት በላይ ሆኖ፤ ወያኔ የፈለገውን ያህል ቢጥር፤ በዘር በሃይማኖት አንከፋፈልም፤ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆንን አንድ ህዝብ ነን በማለት እምቢታውን በማሰማቱ፤ በቀጥታና በተዘዋዋሪ፤ በጋምቤላ፤ በቤንሻንጉል፤ በቴፒ፤ በመቱ፤ በጅማ፤ በአርሲ፤ በአዋሳ፤ በሃረር፤ በወለጋ፤ በጎንደር፤ በወሎና፤ በሌሎችም አከባቢዎች፤ የሰው ልጅ በግፍ እንዲጨፈጨፉ ‘Crime Against Humanity’ ሁኗል። በተለያየ ጊዜ፤ በግልም ይሁን በመደራጀት፤ የነፃነትና የመብት ጥያቄ ያነሱ ሁሉ፤ ታፍነዋል፤ ተገድለዋል፤ ታስረዋል ተሰደዋል።

- ⇒ ‹አብዮታዊ ዲሞክራሲ› የሚል የተዳቀለ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም በማውጣት፤ ኢትዮጵያችን ፤ ከ18 ዓመት አገዛዝ በህዋላ፤ አሁንም የልመና አቁማዳ በመያዝ ፈረንጅ ፊት የምትቀርብ ሀገር አድርገዋታል።
- ⇒ በተሳሳተ የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲ፤ ገበሬው በችጋር እንዲረግፍ፤ የሰው እጅ ጠብቆ የሚኖርና አንገቱን የሚደፋ እድርገውታል።
- ⇒ የኑሮ ውድነት፤ በፍጥነት ሽቅብ እየገሰገሰ ሲሆን፤ በተቃራኒው የከተሜው የወር ገቢ፤ ለዕለት ጉርሱ የማይበቃ ሁኖ፤ እንደ ነገሩ እንደ ነገሩ፤ በፈጣሪው ቸርነት እንዲአድር ሆኗል።
- ⇒ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹አደገኛ ቦዘኔ› ብለው የጠሩት ሥራ አጥ የሃገሬ ሰው፤ ከቀን ወደ ቀን እየጨመሩ በመምጣቱ፤ ሰርቶ የማያድረውና የሰው እጅ የሚጠብቀው፤ ሰርቶ ከሚያድረው በጣም የበዛ ሁኗል። ለባለሙያተኞች ሥርቶ ለማደር፤ መመዘኛው፤ በመያዉ የዩኒቨርስቲ ምሩቅ መሆኑ ቀርቶ፤ በውድም ይሁን በግድ፤ የወያኔ አባልነት ካርድ መያዝ ሆኗል።
- ⇒ ምሁሩን በተለያየ ምክንያት ስም በመስጠትና በማሸማቀቅ፤ በሀገሩ ሰርቶ እንዳያድር በማድረግ፤ በነቂስ እንዲሰደድ ተደርጓል።
- ⇒ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት በሚል፤ የቀድሞ ሶቭየት ህብረት ቦልሸቪክ ፓርቲ፤ ቅጂ

**አንብበው ለወገን ያሰተላልፉ**

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# አሁን ካልተነሳን መቼ ? እኛ ካልተነሳ ማን ?

## ርዕሰ አንቀጽ

ላለፉት ስድት ሳምንታት በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የደረሰዉ ግፍ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ የሚታወቅ ነዉ። የ34 አመት ወጣት የሆነችዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሃሌ የምትባል



የአራት አመት ሴት ልጅ እናት የሆነች ሲሆን የ74 አመት እናት ጧሪ ናት። በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዳ በየካቲት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋል ለፍትህ የነበራት ግንዛቤ ከፈኛ በመሆኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብታ በሕግ ዲግሪ ተመርቃለች። በፌደራል ፍ/ቤትም ዳኛ ሆና ያገለገልች ሲሆን በዳኝነት ሥራዋ የሕግ የበላይነትን በትክክል ሥራ ላይ በማዋል ረገድ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፋለች። በዚሁ ወቅት የ3ኛ ችሎት ዳኛ ሆና የቀድሞዉን የመከላከላይ ሚኒስቴር አቶ ስዬ አብርሃን በዋስ እንዲለቀቁ ብይን በመስጠቷ ከፀጥታ ኀይሎች ከፍተኛ እንግልት ደርሶባትታል።ሕግ የበለያ መሆን እንዳለበት በሥራዋ ያስመሰከረችዋ ዳኛ ብርቱካን ከአገዛዙ በሚሰጥ መመሪያና ብያን አልቀበልም በማለት ከዳኝነት ቦታዋ ለመልቀቅ ተገዳለች።

በሃገሪትቱ ዉስጥ የሕግ የበላይነት በወረቀት ላይ ብቻ የሰፈረ፣ በተግባር ግን ፍትህ የሌለ መሆኑን የተገነዘበችዉ ብርቱካን የፖለቲካዉ ሥርዓራት ካልተሻሻለ የሕግ ሥርዓቱ ከመንግስት ነጻ ሊሆን እንደማይችል አጥብቃ ስላመነች «በሰላማዊ ትግል ለዉጥ ማምጣት ይቻላል» ስትል ፖለቲካዉን በይፋ ተቀላቀለች። ቅንጅት ከተፈጠረ በኋላ የፓርቲዉ ምክትል ሊቀመንበር በመሆን ለፓርቲዉ አሸናፊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች።አሁን ደግሞ የቅንጅት ራዕይ ወራሽ የሆነዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ናት። «ሰዉ ያለነጻነቱ ምንድን ነዉ፤ ያለችዉ ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ የሚያደርገዉን ሰላምዊ ትግል እየመራች ያለችና መክፈል ያለበትን መሥውዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋች ቆራጥ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ መሪ ናት። በአፊሪካ ብቸኛ የሴት ፖለቲካ መሪ ወ/ት ብርቱካን ስትሆን ይህም የጾታ ጭቆና አሁን በበዛባት አህጉር ለሚኖሩ ሴቶች ትልቅ ምሳሌና አርዓያነት የሚሰጥ ነዉ።

የምርጫዉን መጭበርበር ተከትሎ የመጣዉን የሕዝብ ሰላማዊ ተቃዉሞ በኃይል በመጨፍለቅ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንጹህ ዜጎች በአደባባይ ተጨፈጨፉ፣ ከቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላትና ደጋፊዎች ጋር ብርቱካን ሚደቅሳ በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ለእሥር ተዳረገች። ለሃራ ወራት በግፍ በቃሊቲ ከታሰረች በኋላ በአገር ሽምግልና ባህል በተደረገ የይቀርታ ሥርዓት በነሐሴ ወር 1999 ተፈታች።

የምታደርገዉ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስላሰጋቸዉና በፈጠራ ወንጀል ለአራባ 4 ቀናት ከሕግና ከስርዓት ዉጭ በሆነ ወከባ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ተወስዳ መስኮትና ብርሃን በሌለበት ጠባብ ክፍል ዉስጥ ታስራለች። በገዢዉ ፓርቲ «ቶርቸር» ከፍተኛ ግፍ እየደረሰባት ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችዉ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓአት እንዲገነባ፣ ሕግ የበላይ እንዲሆንና የኢትዮጵያ አንድነት እንዲጠበቅ ነዉ። የብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር በኢትዮጵያዉያን ሁሉ ላይ እንደደረሰ ግፍ ተደርጎ የሚቆጠር ነዉ። በወጣትነቷ በእናትነቷና በጧሪነቷ ለአገራችን ሆነ ለአፍሪካ የተቃዉሞ የፖለቲካ ትግል ብርቅዬ የሆነቸዉን ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ ለማስፈታት ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ ለማበርከት መነሳት አለብን። አሁን ካልተነሳን መቼ ? እኛ ካልተነሳ ማን ?

በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ያልታሰሩ የአንድነት ለዲሞርካሲና ለፍትህ ፓርቲ አመራር አባላት በሊቀመንበሯ ላይ የሚደርሰዉን ግፍ ለሕዝብ እያሳወቁና ሕዝብን በሰፊዉ እያደራጁ ነዉ። ከምዕራባዉያን ዲፕሎማትች ጋርም ሰፊ ዉይይት እያደረጉ ሲሆን የምእራባዉያን መንግስታት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለሕወሃት በየአመቱ የሚያበረክቱ እንደመሆናቸዉ ጠንከር ያሉ መልእክቶችን ማስተላለፍ እንዳለባቸዉ እየተናገሩ ነዉ። ለለዚሁ ለምእራባዉያን ዲፕሎማቶችም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያሉበትን የከፋ ሁኔታ በየጊዜዉ እያስረዱ ነዉ።

በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን የትግሉ አካል እንደመሆናችን እኛም ግፍ በኢትዮጵያ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን የበለጠ ጉልበታችንን ማጠንከርና ገዢዉን ፓርቲ ማጋለጥ ይጠበቅብናል።

ዋና የትግሉ አካልም የሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ናቸዉ። ሰላማዊ ሰልፎች በሰላማዊ ትግል ዉስጥ ትልቅ ሚና የሚሰጣቸዉ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ አራት አበይት ጥቅሞች አሏቸዉ።

የመጀመሪያዉ ጥቅም ኢትዮጵያዉያን በአገራቸዉ የሚደርሰዉ ግፍ በመስማት ብቻ በቤታቸዉ ዉስጥ ዉስጡን አይቃጠሉም። ንዴታቸዉን፣ ብሶታቸዉንና ተቃዉሟቸዉን የሚያሰሙበትት እድል ይፈጥርላቸዋል።

ሁለተኛዉ ጥቅም ተከታታይ ሰላማዊ ሰልፎች በተደረጉ ቁጠር የገዢዉ ፓርቲ ግፍ እንዳይረሳና አደባባይ እንዲወጣ ይደረጋል። የተለያዩ ጋዜጦች፣ ሬዲዮ ጣቢያዎች ሰልፎችን በሚዘግቡበት ጊዜ የበለጠ ሰዉ ወደ ትግሉ እንዲቀላቀል ይረዳል። ኢትዮጵያዉያን በተቀናጀ መልኩ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ደግሞ ለገዢዉ ፓቲ ራስ ምታት ብሎም የመወገጃዉ ምክንያት ይሆናሉ።

ሶስተኛዉ የሰላማዊ ሰልፎች ጥቅም በኢትዮጵያ ላለዉ ሕዝባችን ጥንካሬና ተስፋ የመስጠቱ ጉዳይ ነዉ። ሕዝባችን ሕገ መንግስቱ እንደሚያዘዉ እንዳይሰበሰብ፣ ሰልፍ እንዳይወጣ ታግዷል። ህዝባችን ታስሯል። ለታሰረዉ ሕዝባችን ድምጽ የምንሆነዉ በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን ነን። እኛ ስንቀሳቀስ የሕዝቡ ሞራል ይታደሳል።

አራተኛዉና የመጨረሻዉ ጥቅም የምዕራባዉያን ባለሥልጣናት ሕወሃት በሕዝብ የተጠላ፣ ትልቅ ተቃዉሞ እንዳለዉ እንዲረዱ ከማድረጉ በተጨማሪ በኢትዮጵያ የሚደረጉ የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ሊረዳ ይችላል ፡፡ በተለይም በሰልፎቹ በርካታ ኢትዮጵያዉያን የሚገኙ ከሆነና ሰልፎች በተቀናጀ መልኩ በተከታታይነት የሚደረጉ ከሆነ ተጨባጭ ለዉጥ የማምጣቱ እድል የሰፋ ነዉ።

በዚህም ምክንያት በዋሺንግትን ዲሲ በማርች ሁለት 2009 ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ተዘጋጅቷል። በዚህ ሰልፍ በዋሺንግትን ዲስ፣ ሜሪላንድና ቨርጂኒያ አካባቢው የምንኖር ኢትዮጵያዉያ እንድነገኝ፣ ዘመድ ወዳጅ በዚያ አካባቢ ያለን ደግሞ ማበራተቻ እንድንሰጥ ያስፈልጋል።

ሰልፍ ለዉጥ እንደማያመጣ፣ ትርፉ ድካም እንደሆነ የሚናገሩና የሕዝቦ የትግል ስሜት የሚጎትቱ አካላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታወቃል፡ ነገር ኢትዮጵያዉያን በሽንፈት መንፈስ ሳይሆን በ»ይቻላል” መንፈስ የምንቀሳቀስበት ጊዜ ነዉ። አማራጫ ሳያቀርቡ የምናደርገዉን ለሚያሳንሱብን ሰዎች ቦታ መስጠት የለብንም። ለአገራችን ፣ ለሕዝባንች የምንቆምበትና የምንነሳበት ጊዜዉ አሁን ነዉ። አሁን ካልተነሳን መቼ ? እኛ ካልተነሳ ማን ?

### ከልቧ ላይፋቅ ማንም ላያሸራት፣

ቡርቱካን ፤ቃልሽን ለውጪው አትበሏት።

እውነት ጨብጣ ነው ፊትም አነሳሷ፣
ከቃሏ ጋር አብራ ትሞታለች እሷ።

እንኳን ታክሎበት የሙያ ምግባሯ
በቃል የጸና ነው ወገናዊ ፍቅሯ።

ገና ከጅምሩ መድረኩን ስትረግጥ፣
ብርቱካን ምላለች ቃሏን ላትለውጥ።

የቃል ኪዳን እዳ ይዛለች አደራ፣
ላገሯ ነጻነት ልትቆም ልትሰራ።

እልቧ ያለውን ያን ቃሏን ቀምቶ፣
ሊወስደው አይችልም ማንም አስፈራርቶ።

ፍጹም ላያግዳት ላይበግራት እስር፣
ለቃሏ እንደምትሞት ተናግራ እኮ ነበር።

በሃሰት ውንጀላ እናንተው አስራችሁ፣
ሽምግሉን በማለት እናንተው ፈታችሁ፣
ያንን እኩይ ተግባር ያን የሃሰት ወንጀል፣
ከስር መሰረቱን እውነት ለማስመሰል፣
እንደልማዳችሁ ብታስሩ ብትገሉ፣
ስጋ ነው ፈራሹ ሞቶ አይቀርም ትግሉ።

ስለዚህ አትልፉ! ቃል ልታስለውጡ፣
ለሃሰት ቆማችሁ እውነት አትቀላውጡ።

መገኛ ቦታውን ስፍራውን ስታውቁ፣
ከእውነተኛ ሰዎች ሃሰት አትጠብቁ።

ምንም ቢኮመጥጥ ባይጥማችሁ ቃሉ፣
እውነትን በሃሰት ለውጡት አትበሉ።

እንኳንስ በዕውነት በሃሰት መለከፍ፣
ጸንቶ ባያጸናም ታይቷል ሲያስክለፈልፍ።

ከዕውነተኛ ዳኛ ያውም ከታጋይ ሴት፣
ልታገኙ አትችሉም ብትፈልጉ ውሸት።

እንዳሁኑ ጊዜ እንዲህ እንደናንተ፣
ለተንኮል ተውልዶ በተንኮል የሞተ፣
የፍጡር ጭቅቅት ጠባየ ጠምዛዛ፣
ወትሮም ከጥንት አለ ቁጥራቸው ሳይበዛ።

ጊዜን ጊዜን ወልዶ ታሪክም ታሪክን፣
ዘመን እንዳስረዳን የመኖር ሚስጥሩን፣
ካዳም ዘመን ወዲህ ዘርፉ ተያይዞ፣
እናንተ ላይ  ደርሷል ተጉዞ ተጉዞ።

ነገር ግን እስካሁን በእጅጉም  ብትለፉ፣
አትችሉም ካለም ላይ ሃቅን ልታጠፉ።

ብርቱካን ሚደቅሳም ያበራችው ሻማ፣
እንዲሁም የቴዲ የትግል አላማ፣
እንኳንስ በመለስ በነግርማ ፊርማ፣
በልዑል ዳኝነት የፍርድ ቁልመማ፣
በማንም የምድር ሃይል አይችልም ሊቀማ።

ስለዚህ ሁላችን በአንድነት ቆመናል፣
እወቁት እንግዲህ እኛም ቃል ገብተናል።

# ለወቅታዊ ጥያቄ...

ከገጽ 1 የዞረ

የፓርቲውንና የመንግስትን መዋቅር፣ በአንድ በማጣመር፣ በፓርቲውም ይሁን በመንግስት፣ ዲሞክራሲያዊ አሰራርን በመገደብ፣ እንዲሁም፣ ልማታዊ መንግስት በሚል፣ የግል ባለሃብቶችንና የሲቪክ ማህበራትን እንቅስቃሴ በመገደብ፣ ሀገራችንን፣ ቁልቁል የምትጓዝ አድርገዋታል።

በዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ውስጥ፣ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ፣ ህዝቡ በየጊዜው በመደራጀት፣ ገዢውን የወያኔ መደብ፣ በአልገዛም እምቢተኝነት እየተፋለመው ይገኛል። በተለይም፣ በ1997 ዓ ም በቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ አስተባባሪነትና መሪነት ከዚያ ቀደም ታይቶ የማይታወቅና በብዙሃን ዘንድም ያልተገመተና ያልተጠበቀ ከፍተኛ ድል ተቀናጀ። ይሁንና ዕለቱኑ፣ ወያኔ ደርቦት የነበረውን የይምሰል ካባ አሽቀንጥሮ በመውርውር፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ህገ-መንግስቱ ከሚፈቅድላቸው ውጭ፣ 'ጣት ትቀስሩና ጣት እቆርጣለሁ' የሚል አፋኝ አዋጅ አወጡ።

እዚህ ላይ፣ ለቀጣዩ ትግል ይረዳን ዘንድ፣ የ1997ቱን ጨምሮ፣ ከወያኔ ጋር የሚደረጉ ህዝባዊ ግብግቦችና ትግሎች ለምን ተፈላጊውን ውጤት አላመጡም ብለን፣ መመርመርና መወያየት ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁኝ። ለውይይትም ይረዳ ዘንድ በበኩሌ የተገነዘብኳቸውን ላካፍላቹህ እወዳለሁኝ።

## የመተባበር ጥያቄ

አንድ አንድ ወገኖች፣ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ የመስራት ችሎታ የላቸውም ይላሉ። እንደምሳሌም፣ - እጅግ የበረከቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያነሳሉ። በሀገር ቤት በህጋዊነት ተመዝግበው 'በመንቀሳቀስ' ላይ ያሉ 89 የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ የሚበዙት፣ በወያኔ ተጠፍጥፈው የተሰሩና የወያኔ ሎሌ ተብለው ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው። በዲሞክራሲያዊ ትግል ሂደት ውስጥ እዚህ ግባ ሊባል የሚችል አስተዋፅኦ የማያበረክቱ ሲሆን፣ በደፈናው እርባና ቢስ ብለን ልናልፋቸው የምንችላቸው ናቸው።

ሌሎቹ ደግሞ፣ በብሄር በቋንቋ ወይም በክልል የተደራጁ ሆነው፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ በተናጠል፣ ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋፅኦ የተገደበ ነው። ይባስ ብሎም፣ ለአንድ ብሄር ሁለት ሶስት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ይመሰርቱና፣ ጊዜያቸው የሚጠፋው አንድም እርስ በእርስ በመናቆር፣ አልያም ለመዋሃድ በሚያደርጉት ጥረት ነው። ይህም በእራሱ፣ ለዲሞክራሲ የሚያደርጉትን የትግል ጊዜ የሚሻማና አቅማቸውንም የሚያሳንስ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ ህብረ-ብሄር ተብለው የተቋቋሙት ድርጅቶችም፣ እስከ አሁን ድረስ፣ አንድ የነበሩት ሲለያዩ /ቅንጅትን ልብ ይሏል/፣ ሌሎችም ከአቅም አንፃር ትናንሽ የሆኑ፣ በመተባበር ለመስራት ያደረጉት ጥረትም፣ በተለያዩ ምክንያቶች፣ ያልሰመሩላቸው ናቸው። ለመበታተኑም ይሁን በመተባበር ላለመስራት አበይት ምክንያቱ፣ የመርህ ወይም የአካሄድ/የትግል ስልት/ ልዩነት ሳይሆን፣ ግለሰቦች እራሳቸውን ከሀገርና ከድርጅት ጥቅም በላይ በማድረግ፣ የእገሌ ፓርቲ ተብሎ እንዲጠራ ካላቸው ፍላጎትና በድርጅቱ ውስጥ ፈላጭ ቆራጭ የመሆን አዝማምያ ስላላቸው ነው።

በጋራ እና በመተባበር ላለመስራት የያዘን አባዜ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ የተገደበ አይደለም፣ እዚህ እናንተ ባላችሁበት የዋሽንግተን ዲሲ ከተማ እንኳን፣ የዚህ ወይም የዝያ ብሔረሰብ ቤተክርስትያን፣ ይባስ ብሎም፣ የእገሌ ቤተክርስትያን እየተባለ፣ የሃይማኖት ድርጅቶችም ሲከፋፈሉ ይታያሉ። ከሬድዮ ጣብያም አቅም፣ አንድ አዲስ የራድዮ ጣብያ ያየን እንደሆን፣ ያንን የሚቃወም ሌላ ራድዮ ለመጀመሩ ከወዲሁ ተወዳድሮ ማሸነፍ ይቻላል።

## ወገኖቼ

እዚህ ላይ፣ ለእናንተ እዚህ አዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰባችሁት፣ ይህንን ስብሰባ በተለያየ መንገድ ለሚከታተሉትና ይህንን ፅሁፌን ወደፊት ለሚያነቡት ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣ ያለማወላወል፣ ያለመደናቀፍ፣ በሙሉ አንደበቴ፣ ፍፁም እርግጠኛ በመሆን ለመናገር የምችለው ቁም ነገር ቢኖር፣ ተባብረን ካልሰራን በስተቀር፣ የምንናፍቀው፣ ነፃነት ፍትህና ዲሞክራሲ፣ ሰላምና ብልፅግና በሀገራችን መምጣት ህልም ሁኖ እንደሚቀር ነው። በሀገር ቤት የሚገኙ ወገኖቻችን በወያኔ የጭካኔ በትር፣ እነደተገደሉና እንደታሰሩ ይቀጥላሉ፣ እኛም ሀገራችንን እንደናፈቅን ስደተኛ ሁነን እንቀራለን።

እዚህ ላይ መተባበር ስል፣ እያንዳንዱ ድርጅት ቆሜለታለሁ ከሚለው ዓላማው እየቀረፈ በመተው፣ የአደረጃጀት ሰልቱን በመለወጥ፣ የትግል ስልቱን በመቀየር፣ ፍፁም አንድ በሆነ ድርጅት ተውጠው ይስሩ ለማለት ፈልጌ አይደለም። ይህ ሁኔታ፣ ዲሞክራሲያዊ ካለመሆኑም በላይ፣ የሚፈለገውን ውጤት ያመጣል የሚል ዕምነት የለኝም። በመተባበር እንስራ ስል ግን፣ የኔ የግል ዕምነትም ሆነ የምደግፈው ድርጅት ዕምነት፣ የወያኔን መንግስት ተባብሮ ከመጣል የዘለለ አብዛኞዎቹን ድርጅቶቸ ሊያስተባብሩ የሚችሉ፣ መልስ የሚሹ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ስላሉ ነው። በነዚያ ጥያቄዎች ዙርያ፣ እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅታና ህዝባዊ ድርጅቶች፣ እጅ ለእጅ ተያይዘው መስራት ቢችሉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከ9 ወር በላይ አርግዞ የያዛት፣ የምንናፍቃት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መወለጃ ጊዜ አጭር ይሆናል።

## የፍርሃትን ሳይሆን የተስፋን ፖለቲካ ማራመድ

የምንመኛትንና የምንናፍቃትን ኢትዮጵያን ዕውን ሁና ለማየት ያልቻልንበት ሌላው አብይ ችግር፣ በወቅቱ መንግስትም ይሁን የተቃዋሚ ፓርቲዎች በፍርሃት ተሸብበው፣ ህዝቡንም እንዲፈራ ማድረጋቸው ነው።

ወያኔ ፈርቷል። ትልቁ ፍርሃቱ፣ ህዝቡን ነፃ ብለቀው በምርጫ ኮሮጆ ያስወግደኛል የሚል ነው። ለዚህም ነው፣ ልማታዊ መንግሥት፣ በሚል ማደናገርያ፣ ለሚቀጥሉት 50 ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆያት የሚያስችል ስትራተጂ የቀየሰው። በዚህ ፅንሰ-ሀሳብ መሰረት፣ «ኢትዮጵያ ታዳጊ ሀገር እንደመሆኗ፣ የሚያስፈልጋት፣ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የምድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ሳይሆን፣ የአሀዳዊ ፓርቲ ሥርዓት ነው» ብሎ ተነስቷል። ይህ ፓርቲ፣ ወያኔ መሆኑ ነው፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚበጀውን የሚያውቅ፣ ያንንም እየሰፈረ ለህዝብ የሚያድል ነው። ባለሃብቶች፣ ልማታዊ መሆን አለባቸው፣ በወያኔ ሃሳብ ካልተስማሙ፣ ኪራይ ሰብሳቢ ተብለው በመፈረጅ፣ እንዲወገዱ ይደረጋል። ወያኔ ለህዝብ የሚበጀውን የሚያውቅ ብቸኛ አካል እንደመሆኑ መጠን፣ ለህዝብ መድረስ ያለበትን ኢንፎርመየሽን ይወስናል። ሀገራችን በኢንተርኔት ተጠቃሚ ከጎረቤት ሶማልያ እንኳን ያነሰች መሆኗ፣ የአቅም ጣያቄ ሳይሆን፣ የልማታዊ መንግስት ስትራተጂ ውጤት ነው። የሲቪክ ድርጅቶችና ማህበረሰቦች፣ ልማታዊ በመሆን ከወያኔ ጎን መቆም የማይችሉ ከሆነ፣ ከኪራይ ሰብሳቢዎች ጋር ይመደባሉ፣ በአዋጅም ገደብ ይጣልባቸዋል።

ተቃዋሚዎችም ፈርተዋል። የተቃዋሚዎች ፍርሀት የሚመነጨው፣ ከገዥው መደብ ባህርይ ነው። በወያኔ ተጠፍጥፈው የተሰሩ፣ ወይም በሂደት ሙሽራ አድማቂ ብቻ ሆነው የቀሩ ፓርቲዎችን ካልሆነ፣ ወያኔ እንደማያስተናግድም ሆነ እንደማይታገስ በተግባር አሳይቷል። በዚህም ምክንያት፣ በተቃዋሚነት የተሰለፉ አንድ አንድ ፓርቲዎች ወይም፣ በፓርቲ ውስጥ ያሉ አመራሮች፣ 'በጥንቃቄ' መጓዝን የመረጡ ይመስላሉ። የዚህ ጉዞ ውጤቱ፣ የኮክቴል ግብዣን አድማቂ ከመሆን ያለፈ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈይደው ቁም ነገር እንደማይኖር፣ ለሁሉም ግልፅ ሊሆን ይገባል።

## የተግባራዊ እንቅስቃሴ ጥያቄ

ከላይ ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት፣ የወቅቱ ጥሪ የትብብር ጥሪ ነው። መተባበር በራሱ ግን፣ በቂ አይደለም። እነዚህ የተባበሩት ሀይሎች፣ ለህዝብ ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት አለባቸው። በደርግ ጊዜ 'ፈጣን ነው ባቡሩ' የሚል ቀስቃሽ ሙዚቃ ይዘመር ነበር። ባቡሩ ጣቢያውን ከለቀቀ ቆይቷል። ለመቆም፣ ለማዝገም፣ ለመቆዘም፣ ለመፍራት ጊዜ የለም። እስከ ዛሬ ድረስ፣ በአብዛኛው፣ ስንሰበሰብ ስንወያይ እቅድ ስናወጣ፣ ትግሉን ዳር ዳሩን ስንዞረው ቆይተናል። አሁን ወቅቱ፣ ትግሉን በቆራጥነት የምንገባበትና የምንገፋበት ወቅት ነው። ወያኔ፣ ለግፉ መብዛት አንዱ ምክንያቱ፣ ህዝቡ ምን ያመጣል፣ እስከ አሁንስ ምን መጣ በሚል ትዕቢት ነው። እራሱ ፈርቶ፣ ህዝቡን አስፈራርቷል። ፈረንጆች፣ " Every People Will Have a Government They Deserve" ይላሉ። የሀገራችን አዋቂዎችም፣ 'ጎረቤት ሲታማ፣ እህ ብለህ ስማ' ይላሉ፣ ነግ በኔ ለማለት ሲፈልጉ።

እስከ ዛሬ ድረስ፣ ጋምቤላ ተመታ ሲባል እህህ ስንል፣ ቤንሻንጉል ተመታ ሲባል እህህ ስንል፣ በወለጋ ህዝብ ተጨፈጨ ሲባል እህህ ስንል፣ ጎንደሬ ተረሸነ ሲባል እህህ ስንል፣ የኦጋዴን ህዝብ በአይሮፕላን መላወሻ አሳጡት /Carpet Bomb/ ሲባል እህህ ስንል፣ እገሌ ተገደለ፣ እገሊት ታሰረች፣ እነ እገሌ ተሰደዱ ሲባል፣ ህመማቸው ሲያመን፣ ጉዳታቸው ሲሰማን፣ ዕምባችንን አምቀን ለቅሶዋችንን ወደ ውስጥ ስናለቅስ ከርመናል።

ከአሁን በህዋላ ግን ‹በቃ› ማለት መቻል አለብን። ህዝብ መደራጀት አለበት። ዝምታ ይብቃ። ወያኔዎች 'Silent' የሚሉት 'Majority' ድምፁን ማሰማት ብቻ ሳይሆን፣ ለወንዱሙና እህቱ የድረሱልኝ ሰቆቃ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት መቻል አለበት። ጊዜው አሁን ነው። ወደ ድል ሊወስዱን የሚችሉ ስልቶች ባጠቃላይ መተግበር አለባቸው። እንደተለመደው፣ በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ጮሆ መግባትና ስብሰባ ሲጠራ መምጣት፣ ወይም ደግሞ ያለኝን ሰጥቻለሁኝ ከዚህ በላይ አይጠበቅብኝም በሚል ሳንቲም መወርወር፣ በቂ አይደለም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለትግል የሚጠራ ሳይሆን፣ የትግሉ ባለቤት መሆን መቻል አለበት። ወቅቱ የሚጠይቀው የትግል ስልት፣ ዜጎችን በአንደኛ እና በሁለተኛ ረድፍ የሚያሰልፍ ሳይሆን፣ ሁሉም ለትግሉ ግንባር ቀደም ተሰላፊ መሆን ማስቻል አለበት።

በተለይም በሀገር ቤት፣ የትግሉ ዋንኛ መድረክ እንደመሆኑ መጠን፣ የህዝብ ተሳትፎ ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በተናጠል፣ እዚህም እዝያም የሚደረጉ፣ መፍጨርጨሮች፣ በውጤታቸው፣ አላስፈላጊ የሆኑ መስዋዕትነቶችን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለወቅታዊ ጥያቄ...

ከገጽ 3 የዞረ

የሚያስከፍሉ ሲሆኑ፣ ለወያኔ ደግሞ የልብ ልብ የሚሰጡ ናቸው። የትግል ስልቱን ከመቀየስ ጀምሮ፣ በትግሉ ላይ ንቁ ተሳታፊ እስከመሆን ድረስ ህዝቡ መንቀሳቀስ መቻል አለበት። የህዝብ ሀይል አምባገነን መሪዎችን ማንበርከክ ለመቻሉ፣ ታሪክም ሆነ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እየተካሄዱ ያሉት ትግሎች ጉልህ ማሰረጃዎች ናቸው። “ጨለማን ዘላለም ከመፍራት፣ ቁራጭ ሻማ መለኮስ” ይላሉ አበው ነገርን በምሳሌ ሲያስረዱ። እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከታሰረበት የፍርሃት ገመድ ተላቆ፣ የየራሱን ቁራሽ ሻማ ከለኮሰ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያችን የነፃነትን፣ የፍትህንና የዲሞክራሲን ችቦ ማንቦግቦግ እንችላለን።

በዚህ የትግል ወቅት፣ በድርጅት የገቡና አመራሩን የያዙ ሰዎች፣ ከማናችንም የላቀ እንቅስቃሴ ይጠበቅባቸዋል። ብልህነት፣ አስተዋይነት፣ አርቆ አሳቢነት ከሁሉም በላይ ግን ቆራጥነት፣ ከነሱ እንጠብቃለን። ህዝብ ከህዋላቸው ብቻ ሳይሆን ከዙርያቸው እንዳለ መረዳት አለባቸው። ይህን የህዝብ ሀይል፣ የህዝብ ማዕበል፣ በብልህነትና በቆራጥነት መምራት ከቻሉ፣ ትግሉን ከግብ ማድረስ ለመቻላቸው ምንም ጥርጥር የለኝም። እነሱም አደራቸውን ተወጡ ማለት ነው። ከመሪዎቻችን የምንጠብቀውም ከዚህ ያነሰ አይደለም።

የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነቸው ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ከሁሉም ቀድማ፣ በህጋዊና ሰላማዊ ትግሉ እምነት አሳድራ፣ ሀገር ቤት ስትመለስ፣ የወያኔን የጠመንጃ ብዛት በኪሎ መዝና፣ የአጋዚ ጦርን ብዛት ቆጥራ፣ ልታገለው እችላለሁ ብላ አይደለም። በአንድ የወያኔ ጀሌ፣ በአንድ ጥይት ብቻ፣ የሷ ሕይወትዋ ሊያበቃለት እንደሚችል፣ ፍፁም ትረዳለች። በሌላ በኩል ደግሞ፣ የወያኔን ልብ መርምራ ርሁረህ ነው፣ አይጨክንብንም፣ አይገድለንም አያስረንም፣ በሰላማዊ ትግል እንድንንቀሳቀስ ፈቃዱ ነው ከሚል የዋህነት የመነጨም አይደለም። የወያኔን ልብ መመርመር ሳያስፈልጋት፣ ስራውን በተግባር አይታዋለች። ይልቁንም፣ እሷ ተስፋ ያደረገችው፣ ሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ህዝቡ መረረኝ በቃኝ ካለ፣ ለመታገል ከወሰነ፣ተስፋ ካልቆረጠ፣ በይቻላል መንፈስ በአንድነት ከዳር እስከ ዳር ከተንቀሳቀሰ፣ እኔና ከእኔ ጋር በአመራርነት የተሰለፍነው መስዋዕት ለመሆን ብንችልም እንኳን፣ በሀገሬ፣ ህዝቤ አንድ ቀን በነፃነት ይኖራል፣ ፍትህ ይሰፍናል፣ ዲሞክራሲ ያብባል ብላ በማሰብ ነው። ብርቱካን በዚህ ዕምነቷ ብቻ፣ የህሊና እስረኛ ሆና ቃሊቲን ቤቷ ካደረገች፣ 2 በ 2 በሆነ ጠባብ የቆርቆሮ ቤት ከተዘጋባት እነሆ፣ ሳምንታት አለፉ።

በወያኔ እስር ቤት የገባችው ብርቱካን ብቻ አይደለችም፣ የኦፍዴን ዋና ፀሃፊ አቶ በቀለ ጅራታ ዕውቁ የኪነት ባለሞያ ቴድሮስ ካሳሁን፣ አቶ አበራ የማነ አብ፣ ፀጋዬ ገ/መድህን የመሳሰሉ ዕውቅ ታጋዮችን ወያኔ በእስር ቤት አጉሯል። ከነዚህም በተጨማሪ፣ በየቦታው በየፊናቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረከቱ፣ ከፍተኛውን መስዋዕትነት የከፈሉ፣ ይህም ድርጊታቸው ወያኔን ያስቆጣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፣ በየእስር ቤቱ ታጉረዋል። እነዚህ ታጋዮች፣ እንደ ስማቸው ሁሉ፣ ፆታቸው፣ እድሜያቸው፣ ሀይማኖታቸው፣ ብሔራቸው፣ የፖለቲካ አመለካከታቸው ይለያያል። በግፍ ከመታሰራቸው ባሻገር፣ ሌላው አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ግን፣ የወያኔን የግፍ አገዛዝ፣ እምቢኝ ብለው በቀዳሚነት በትግሉ መሰለፋቸው ነው።

## የሀገሬ ህዝብ ሆይ!

እኔ እና እናንተስ፣ ለዚህ የህዝብ ጥግል ጥሪ መልሳችን ምንድነው? በበኩሌ ለተግባራዊ ትግሉ ለመታገል ወስኛለሁ። ተኝቼ እንቅልፍ ላይወስደኝ፣ በልቼ ላልጠግብ ጠጥቼ ላልረካ ለራሴና ለፈጣሪዬ፣ ቃል ገብቻለሁ። ከአንግዲህ፡ ሥራ በዛብኝ፣ ተማሪ ነኝ፣ ቤተሰብ አለኝ፣ ያመኛል፣ የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ላልል፣ ሰበብ ላልደረድር፣ ይኸው እናንተ ፊት ቃሌን አድሳለሁ። እናንተም እንደዚሁ እንድትሉ የትግል ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ለጥሪውም ተግባራዊ ምላሽ እንደማገኝ ተስፋዬ ነው።

እዚህ ላይ አንድ ታሪክ ላጫውታቹህ፣ ፓርቲያችን በደቡብ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ወቅት፣ አንድ ተጋይ ከህዘብ መሃል ይነሱና፣ ቀስቃሽ የሆነ ንግግር ያደርጋሉ፣ አጠገባቸው የነበሩት፣ ‘እንዴት ነው እንዲህ የምትናገረው አትፈራም ወይ’ ብለው ይጠይቋቸዋል። እሳቸውም፣ ‘መታሰርን አልፈራም፣ ብርቱካን የገባችበት እስር ቤት መግባት እንዲያውም ክብር ነው’ ነበር ያሉት።

## ቀጣዩ ትግል

እንግዲህ በትግሉ ለመሳተፍ ቃል ስገባና እናንተም ቃል እንድትገቡ ስጠይቅ፣ በተለይም አመራር በሆንኩበት በሰሜን አሜሪካ የአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበር ምን ታስቧል፣ እጃቹህ ከምን ማለታቹህ አልቀረም።

ማህበራችን ትግሉን በሁለት ከፍሎ ያየዋል።

<u>አንደኛ፤</u> ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ የህሊና እስረኞች በአጠቃላይ እንዲፈቱና ትግሉን መልሰው እንዲቀላቀሉ የሚደረግ ትግል ነው። የብርቱካንና የእስር ጓዶቿ መታሰር፣ በግላቸው ከሚደርስባቸው እንግልትና ወከባ ባሻገር፣ ትግሉን የማያስቀረው ቢሆንም እንኳን፣ እንደሚጎዳው ግን ገልፅ ነው። በሌላ አባባል፣ የብርቱካን ከእስር መፈታት እና፣ ተመልሳ የፓርቲወን አመራር መያዝ፣ ወሳኝ ነው ብለን እናምናለን። ለዚህም ይረዳ ዘንድ፣ ከሌሎች የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመተባበር እየሰራን ያለነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የሚንቀሳቀስ Free Birtukan Mideksa በሚል በስፋት በሚንቀሳቀስ፣ ስብስብ ውስጥ፣ በንቃት እየተሳተፍን ነው። በዚህ ስብስብ ውስጥ የተካተቱት ግለሰቦች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባል የሆኑ፣ እንዲሁም በድርጅት ውስጥ ያልታቀፉ ግን፣ እስረኞችን ለማስፈታት መንቀሳቀስ የፈለጉ ሰዎች ናቸው። በዚህ አጋጣሚ፣ እናንተም በዚህ ስብስብ ውስጥ ገበታቹህ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ስብስቡ እራሱን በተለያዩ ንዑስ ኮሚቴዎች ያደራጀ ሲሆን፣ የእንቅስቃሴው ውጤቶችም፣ በቅርቡ በሂደት በህዝቡ ዘንድ የሚታዩ ለመሆናቸው ጥርጥር የለኝም።

በሀገር ቤት የሚገኘው አንድነት ፓርቲያችንም በተመሳሳይ መልኩ፣ ሊቀመንበሯን ብርቱካንን ለማስፈታት፣ አራት ንኡስ ኮሚቴዎችን አቋቁሞ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። ውጤቱንም በተግባር እንደምታዩት ከወዲህ ላረጋግጥላቹህ እፈልጋለሁ።

<u>ሁለተኛ፦</u> ወያኔ ወ/ት ብርቱካንንና ሌሎች ታጋዮችን ሲያስር፣ ስሌቱ የነሱ መታሰር ትግሉን ከማዳከም አልፎ ጭርሱኑ ይቀጨዋል፣ በዚህም ምክንያት በመጪው 2002 በሚካሄደው ምርጫ፣ ያለተቃናቃኝ ብቻዬን ሮጬ አሸናፊ እሆናለሁ ከሚል ደካማ አሰተሳሰብ ነው። በዚህም ምክንያት፣ ተግባራዊ ምላሹ መሆን ያለበት፣ የብርቱካን መታሰር ሺህ ብርቱካኖችን ፈጥሮ፣ ትግሉን በበለጠ ማፋፋም ነው። የአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበራት በዚህም ዘርፍ፣ በበለጠ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የብርቱካን መታሰር፣ ለትግሉ ‘የገና ስጦታ‘ ነው ብለን እናምናለን። ለጊዜው ተዳፍኖ ይመስል የነበረው እንቅስቃሴ መፋፋም ጀምሯል። ለጊዜው ተስፋ የቆረጠ የመሰለው ህዝብ ተስፋው እንደገና አብቧል፣ ማህበራችንም ይህንን በመገንዘብ፣ ይህንን እምቅ ሃይል፣ በተግባር የሚሰለፍ ሃይል ለማድረግ በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ነው። ከሌሎች ድርጅቶች ጋርም በመተባበር ለመስራት፣ ንግግሩ ተጀምሯል። ንግግሩም ፈር እየያዘ መሆኑን ስናገር በደስታ ነው።

በተመሳሳይ፣ በሀገር ቤት የሚገኘው አንድነት ፓርቲ፣ በማዕከልም ሆነ በማዕዘናት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ገፍቶበታል። ከዚህ በፊት ተከፍተው የነበሩት 35 ቢሮዎችን ማጠናከርና ተጨማሪ 48 ቢሮዎችን መክፈት ተቀዳሚ ተግባሩ አድርጓል። ይህንንም ለማስፈፀም በከፍተኛ አመራሮች የሚመሩ ሁለት የተለያዩ ቡድኖች በሰሜንና በደቡብ የተንቃሰቀሱ ሲሆን፣ ውጤቱም አመርቂ ነው ለማለት ይቻላል። በየሄዱበት ሁሉ፣ የገጠማቸው ‘እኛ ተደራጅተናል፣ ዕውቅና ስጡን፣ የምንጠብቀው የናንተን አመራር ብቻ ነው’ የሚል ነው።

## ወገኖቼ

እንግዲህ፣ ከዚህ አጭር ዘገባዬ ለመረዳት እንደምትችሉት፣ በሀገር ቤትም ከሀገር ውጭም፣ ህዝብ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። በዚህ ወቅት ግለሰቦችም ይሁኑ ድርጅቶች የሚያደርጉት የታሪክ ሽሚያ የለም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፣ አነሰም በዛም ለትግሉ፡ የሚያደርገው አስተዋፅኦ የታሪክ ባለቤት ያደርገዋል። በጋራ ብርቱካንን ነፃ እናውጣ፣ በጋራ የህሊና እስረኞችን በአጣቃላይ ነፃ እናውጣ፣ በጋራ ትግላችን ሀገራችንን ነፃ እናውጣ። ኑ ተነሱ፣ እንነሳ ፣በጋራ ትግላችን ታሪክ እንስራ።

እግዚአብሔር አምላክ ይባርካቹህ!!!

እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያን ይባርክ!!!

አትላንታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴንቨር * ሎሳንጀለስ* ላስቬገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል *
ኦክላንድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፕ ስቴኢት ኒኦርክ *
ዋሽንግትን ሜትሮ

ለአንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ ( ቅንጅት) በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መሀበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna@kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdethiopia@gmail.com
ይጻፉልን